# የመካከለኛው ዘመን ኢትዮጵያ የግእዝ ድርሳናት ፍልስፍናዊ ፋይዳ

ዳዊት ግርማ[1]፣ ሳሙኤል ጌትነት[2]፣

## አኅጽሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዓላማ ዘመን ተሻጋሪ የግእዝ ድርሳናት ላይ ፍልስፍናን ማጥናት፤ የፍልስፍና ድርሳናቱን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ ከፍልስፍና ጽሑፎች ውስጥ *ፊሳልጎስ፣ ስክንድስ፣ አንጋረ ፈላስፋ፣ ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብና ሐተታ ወልደ ሕይወት* በጥናቱ ተካተዋል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሶስቱ የፍልስፍና መጻሕፍት በዘይቤና ተምሳሌት ከፊል ኢትዮጵያዊ ሆነው ተወርሰዋል፡፡ ፍልስፍናዊ ይዘት ያላቸው እሳቤዎች ድርሳናቱ ውስጥ ተዳስሰዋል፡፡ ዲበ አካላዊነት፣ ሥነ ዕውቀት፣ ሥነ አመክንዮ፣ ሥነ ምግባር የመሰሉ የፍልስፍና የጥናት ዘርፎችን እንደንድፈ ሐሳባዊ መቀንበቢያ በመጠቀም በገላጭ ሥነ-ዘዴ የሰነድ ትንተናን እንደ ስልተ ጥናት ይተገብራል፡፡ ድርሳናቱ በጥልቅ ፍልስፍናዊ ይዘት ከመርቀቃቸውም በላይ ለኢትዮጵያ ፍልስፍና ፋይዳቸው ጉልህ ነው፡፡ ዘርዓ ያዕቆብ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ ሆኖ ዘመናዊ ፍልስፍናን እንደነ ዴካርት ካሉ ታዋቂ የምዕራቡ ዓለም ፈላስፋዎች ተነጻጻሪ ሆኖ በኢትዮጵያ ጀምሯል፡፡ ደቀ መዝሙሩ ወልደ ሕይወትም የመምህሩን አስተምህሮ ቀጥሎ የራሱን አሰላስሎት አክሎ አስፋፍቶታል፡፡ ከተጠቀሱት የፍልስፍና መስኮች በተጨማሪ እንስታዊነትና የሃይማኖት ፍልስፍና የሚንጻባረቅበት እሳቤዎችን ሁለቱ ዘመናዊ ኢትዮጵያውያን ፈላስፎች መርምረዋል፡፡ ጥናቱ በጥንታዊ የግእዝ የሥነ ጽሑፍ ስራዎች ውስጥ ፍልስፍና መኖሩን፤ የታወቁት የፍልስፍና ድርሰቶችና ፍልሱፋኑም ከዘመናዊ ፍልስፍና አንጻር ተፈትነው ምሉዕመሆናቸውን አጽንቶ ለሀገራችን የፍልስፍና፣ የጥበብና በነጻነት የማሰላሰል ታሪክም ዘርፈ ብዙ ፋይዳ እንዳላቸው ድምዳሜ ላይ ይደርሳል፡፡

*ቁልፍ ቃላት፡-* የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ የግእዝ ፍልስፍናዊ መጻሕፍት

## መግቢያ

በረጂም ምዕት-ዓመታት የታሪክ ሂደት ውስጥ ለቀደምት ኢትዮጵያውያን በእውቀትና በጥበብ መራቀቅ የታሪካቸው አንዱ መለያ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ የራሳቸው ሥርዓተ ጽሑፍና የፊደል ገበታ ካላቸው ጥቂት በስልጣኔ የቀደሙ የዓለም ሀገራት መካከል አንዷ ናት፡፡ ይህንን ፊደልና የጽሕፈት ባህል በመጠቀም የሀገራችን ሊቃውንት በርካታ ዘመናትን ያስቆጠሩ አያሌ መጽሐፍትን ጽፈው አልፈዋል፡፡ ኢትዮጵያ ከብዙ ክፍለ ዘመናት በፊት የሥነ ጽሑፍ ልማድ ነበራት፡፡ በቅድመ ክርስትና ዘመን የድንጋይ

[1] በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በእንግሊዝኛ *ሥነ* ጽሑፍ የPhD ተማሪ

[2] ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ

ላይ ጽሑፎች የነበሩ ሲሆን፣ ከክርስትና መምጣት በኋላ ደግሞ በለሰለሱ ቁሶች ላይ መጻሕፍት ይጻፉ ጀመር፡፡ እነዚህ የጽሑፍ ውጤቶች ፍልስፍናዊ፣ ሥነ ጽሑፋዊ፣ ሥነ ክዋክብት ጥናት፣ ባህላዊ ህክምና፣ የዘመን አቆጣጠር (ባህረ-ሃሳብ)፣ ሥነ- ሕንጻ፣ ሕግ አስተዳደር ብሎም ልዩ ልዩ የሳይንስና የጥበብ ይዘትና ፋይዳ ያላቸው ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በድንጋይ ላይ በመጻፍ እንደተጀመረ ይታመናል፡፡ በራሳቸው ፊደል የጽሑፍ ባህል ካዳበሩ ጥቂት የዓለማችን ሃገራት መካከል አንዷ የሆነችው አገራችን ለሺህ ዘመናት የዘለቀ ሃገር በቀል የሥነ ጽሑፍ ልማድ ያላት አገር ናት፡፡ ለዚህም በሳባውያንና ሌሎችም ቋንቋዎች ተከትበው በተለይ በአክሱም አካባቢ በቁፋሮ የተገኙ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች (inscriptions) እማኝ ናቸው፡፡ ከዚያም በተለይ ከክርስትና እምነት መሰበክ በኋላ በጠንካራ ቁሶች ላይ ማለትም ድንጋይ፣ ብረት፣ ሸክላ እና እንጨት ከመጻፍ ወደ ለስላሳ ቁሶች ማለትም ብራና ላይ መጻፍ ተጀመረ:: ከ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በግእዝ ቋንቋ መጻሕፍት ይጻፉ ጀመር፡፡ አብዛኞቹ ጽሑፎችም ከቅብጥ፣ ጽርዕ፣ ሱርስት፣ አረማይክ እና ሌሎች ቋንቋዎች የሚተረጐሙ ነበሩ፡፡ በዚያን ዘመን በትርጉሙ ሥራ መሪ ተዋንያን ከነበሩት ውስጥ ተስዓቱ ቅዱሳን እና ቅዱስ ፍሬምናጦስ (አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን) ይገኙበታል፡፡ ይህ የሥነ-ጽሑፍ ሥራ በዘመነ አክሱም የነበረና እስከ ሥርወ-መንግሥቱ ፍጻሜ ድረስ የዘለቀ ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች የአክሱም ስልጣኔ ከወደቀ በኋላ እስከ ዛጉዌ ዘመን መጀመር ድረስ (ከ8ኛዉ እስከ 12ኛዉ ክ/ዘመን) ያለው ጊዜ በታሪክ "የጨለማዉ ዘመን" ተብሎ የሚታወቅና ታሪኩም ሆነ የጊዜዉ ንቅስቃሴ እምብዛም የማይታወቅና ያልተመዘገበ፣ ስልጣኔም ያልነበረበት ዘመን ስለነበር የሥነ-ጽሑፉ እድገትም በእጅጉ የተዳከመ ነበር፡፡

Adamu and Belaynesh (1970)፣ ብዛት ያለው የሥነ-ጽሑፍ ሥራ ከአምስተኛዉ ክ/ዘመን ጀምሮ መውጣት እንደ ጀመረ ይናገራሉ፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ የዘለቀው ጥንታዊዉ የኢትዮጵያ (ግእዝ) ሥነ-ጽሑፍ መካከለኛዉ ዘመን ላይ አብቦ ይጎመራል፡፡ የኢትዮጵያ (ግእዝ) ሥነ ጽሑፍ ታላቅ የእድገት ደረጃ ላይ የደረሰው፣ ያበበው፣ ግሩም ወጥ/ሃገር በቀል የሥነ-ጽሑፍ ስራዎች የተመረቱበት፣ በርካታ ጸሐፍት የበቀሉበት፣ ግሩም የትርጉም ሥራዎች የተሰሩበት፣ ወዘተ ዘመን ነው- የመካከለኛው ዘመን፡፡ በዚህም የተነሣ ከመካከለኛዉ ዘመን 15ኛው መ/ክ/ዘመን በኢትዮጵያ የሥነ-ጽሑፍ ታሪክ "ወርቃማዉ ዘመን" በመባል ይታወቃል፡፡ በመካከለኛዉ ዘመን ግእዝ በጽሑፍ ብቻ ተወስኖ የንግግር ቋንቋነቱን ለአማርኛ ያስረከበበት ወቅት ነበር፡፡ Bender

ስለመካከለኛውን ዘመን ሲናገር "የሥነ ጽሑፉ እድገት ከፍተኛ ጡዘት ላይ የደረሰው ከ14ኛው እስከ 19ኛው ክ/ዘመን ነበር" (Bender et.al., 1976፣ገጽ 97) ብሏል። "ከሰሎሞናዊዉ ስርወ-መንግሥት እንደገና ማበብ በኋላ 14ኛ ክ/ዘመን የኢትጵያ ሥነ ጽሑፍ ዘመን ተብሎ የሚታወቀው ዘመን ጅማሮ ሆነ" (Adamu and Belaynesh, 1970፣ ገጽ 46)። ጎርጎርዮስ (1974[3]) በበኩላቸዉ የመካከለኛዉ ዘመን ታሪክ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠውና ከትርጉም ባሻገር ወጥ ድርሰቶች በተለይ ገድላት መጻፍ የተጀመሩበት ጊዜ መሆንን ይናገራሉ። *"...ከ13ኛዉ እስከ 16ኛው ያሉት ሶስት ተከታታይ ክ/ዘመናት ብዛት ያላቸው ገድላት የተጻፉበት፣ የሥነ ጽሑፉ ትንሳኤ እና እድገት የታየበት"* ነው ይላል (Taddesse, 1970፣ገጽ 14)።

ከ13ኛው መቶ ክ/ዘመን የሚጀምረው መካከለኛው ዘመን በኢትዮጵያ የሥነ-ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው የሚባለው በርካታ መጽሐፍት የተጻፉበት፣ ከትርጉም ውጭ ወጥ መጽሐፍት የተጻፉበት፣ እንዲሁም ታላላቅ ደራሲያን የተነሱበት በመሆኑ ነው። በመካከለኛዉ ዘመን ከተተረጎሙት መጻሕፍት መካከል፡- *መጽሐፍ ቅዱስ፣ ዜና አይሁድ፣ ስንክሳር፣ መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ግብረ ሕማማት፣ ገድለ ሐዋርያት፣ ውዳሴ ማርያም፣ መጽሐፈ ኪዳን፣ ዲዲስቅልያ፣ ገድለ ጊዮርጊስ፣ መጽሐፈ አስቴር፣ መጽሐፈ ኢሳይያስ፣ ደቂቅ ነቢያት፣ ክብረ ነገሥት፣ ፍትሃ ነገሥት፣ ተዓምረ ማርያም፣ ፊሳሎጎስ* እና መሰል ይገኙበታል። በዚህ በመካከለኛው ዘመን ከተጻፉት ገድላት መካከል ደግሞ፡- *ገድለ ተ/ሃይማኖት፣ ገድለ ገ/መንፈስ ቅዱስ፣ ገድለ አባ አረጋዊ፣ ገድለ አባ ጴንጤሌዎን፣ ገድለ አባ ፊሊጶስ፣ ገድለ አባ አኖሬዎስ፣ ገድለ አባ በጸሎተ ሚካኤል፣ ገድለ ይምርሃነ ክርስቶስ፣ ገድለ ላሊበላ፣ ነአኩቶ ለአብ፣ ገድለ መስቀል ክብራ*፣ ወዘተ ይገኙበታል፡፡ ከላይ ስለግእዝ ሥነ ጽሑፍ የቀረበው አጭር ገለጻ የሥነ ጽሑፉ አንዱ ገጽታ ፍልስፍና መሆኑን ለማጠየቅ ብሎም በግእዝ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ያሉትን የፍልስፍና ድርሳናት ለማጥናት እንደመስፈንጠሪያ ይሆን ዘንድ ነው። በመካከለኛው ዘመን ከተጻፉና ከተተረጎሙ ድርሳናት እንዲሁም ከተቀኙ ቅኔያት ውስጥ የፍልስፍና የሆኑና ፍልስፍና ነክ የሆኑ በርካታ አሉ። ፍልስፍና ለሰው ልጆች ኑሮ አስፈላጊ ከሆኑና የእለት ከእለት የህይወት ጓዳን ከምንዳስስባቸው ነገሮች አንዱና ህይወትን በአእምሮ ለመምራት የሚያስችለን ጥበብ ሆኖ እናገኘዋለን። በኢትዮጵያ ጥንታዊ ድርሳናት ፍልስፍና አለ ወይስ የለም የሚለው፤

[3] የደራሲው ስም በአማርኛ ከተገለጸ የዘመን አቆጣጠሩ የኢትዮጵያ፤ በእንግሊዝኛ ከተጻፈ ደግሞ የጎርጎርዮሳውያን መሆኑን ልብ ይሏል።

ብሎም ኢትዮጵያ ውስጥ አልፎም በአፍሪካ ምድር የፍልስፍና አየር ነበር ወይ የሚለው ጉዳይ አነጋጋሪ ሆኖ ለዘመናት ቆይቷል፡፡

የኢትዮጵያን ፍልስፍና በሚመለከት Claude Sumner (1998) አፋዊ (*ሥነ ቃላዊ*) እና ጽሑፋዊ በሚል በመክፈል አፋዊው ፍፁም ኢትዮጲያዊ ሲሆን ጽሑፋዊ የሆኑት ደግሞ ሃገር-በቀልና የትርጉም ውርስ *ሥራዎች* በማለት ይከፋፏቸዋል፡፡ ከትርጉም ስራዎች መካከል ሦስት ስራዎች የሚጠቀሱ ሲሆን የመጀመሪያውና በ5ኛው መቶ ክ/ዘመን እስክንድርያ በሚኖር ኢትዮጵያዊ ከግሪክ የተተረጎመው *ፊሳልጎስ* የተባለው ባለ48 ምዕራፍ አጭር መጽሐፍ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በመካከለኛው ዘመን ከአረብኛ ወደ ግእዝ የተተረጎመው *አንጋረ ፈላስፋ* የተባለው ስነ ምግባርና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገ መጽሐፍ ነው፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው የትርጉም ስራ ደግሞ *የስክንድስ ሕይወትና ስራ* የሚባለው ሲሆን ከአረብኛ ወደ ግእዝ ከተተረጎመው የሆሜር ስራ ከሆነው የ"ኦዲፐስ" ታሪክ ጋር የሚመሳሰል ነው (Sumner, 1981)፡፡ ከላይ ከተገለፁት የትርጉም የፍልስፍና ስራዎች ባሻገር ወጥ የሆኑ አገር በቀል አትዮጵያዊ አስተሳሰብ የተንፀባረቀባቸው የግእዝ የፍልስፍና ስራዎችም ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የዘርዓ ያዕቆብ ስራ የሆነው *ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብ* እና የደቀ መዝሙሩ የወልደ ሕይወት *ሐተታ ወልደ ሕይወት* የተሰኙት ስራዎች ይጠቀሳሉ፡፡ ከላይ የተገለጡት ስራዎች ሃይማኖትን በምክንያት ከመመርመር ባሻገር ተፈጥሮን በአንክሮ በመርመር ሳይንሳዊነታቸው ጎልቶ የሚታዩ ናቸው፡፡

በላይ መኰንን (ሊቀ ኅሩያን) በኤፍሬም ስዩም (2006 ዓ.ም) *ተዋነይ* መጽሐፍ ውስጥ በጻፈው መቅድም ላይ፤ "ፈላስፋ የሚለው ቃል መሰረቱ የግእዝ ቋንቋ ሲሆን ፈልሰፈ፣ አወቀ፣ ተራቀቀ፣ ተጠበበ፣ ብለሀተኛ ሆነ" የሚል ትርጉም ይሰጠዋል፡፡ Branden (1969) በበኩሉ፣ "አመክንዮ" ማለት ሰው ለሆነው ፍጡር ሁሉ ለድረጊቱ ብሎም ለጠቅላላ ህልውናው መሰረት ለሆነው መስተኃልዩ የእሳቤ ሕግ ወይም ስርዓት ነው ይለዋል፡፡ ለዚህም ይመስላል ብርሃኑ ድንቄ (1987 ዓ.ም) በገፀ ባህሪው በኩል የእንግሊዛዊውን ባለቅኔ ሳሙኤል ቴለር ሃሳብ በመውሰድ ታላቅ ፈላስፋ ሳይሆኑ ታላቅ ባለቅኔ መሆን እንደማይቻል የሚያትትልን፡፡ ምንም እንኳ ከላይ በተገለፀው አግባብ የግእዝ ድርሳናት ፍልስፍናዊ፣ ሳይንሳዊና ሥነ ጽሑፋዊ ፋይዳ ቢኖራቸውም የግእዝ ቋንቋ ከማኅበረሰብ የንግግር ቋንቋነት ተገልሎ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚውል ቋንቋ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፤ የትምህርትና የጥናት ሥርዓታችን ከምዕራባውያን ስርዓተ-ትምህርት ላይ የተመሰረተ መሆኑ፤ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ንብረት የሆኑት ድርሳናት በሚገባው ልክ የማስተዋወቅና ለጥናትና ምርምር የማዋል ክፍተት እንዲሁም

የድርሳናቱ በዝርፊያ መጥፋት ጋር ተያይዞ፤ የእነዚህን የሥነ ጽሑፍ ውጤቶች እምቅ ፍልስፍና፣ ሳይንስና ሥነ ጽሑፋዊ ውበት ትሩፋት ለማግኘት ብሎም ባለው ላይ በማበልፀግ ወጥ የሆነ ሃገራዊ ስልጣኔያችንን መገንባት አልቻልንም፡፡ በተለይም ደግሞ እነዚህ የኢትዮጵያ ድርሳናት ሃይማኖታዊ ፋይዳ ባሻገር ፍልስፍናዊ፣ ሳይንሳዊና ሥነ ጽሑፋዊ ፋይዳቸው በልበ ሙሉነት ለመናገር በሚያደፋፍር ሁኔታ መሰረታዊ ጥናት አልተደረገበትም፡፡ ስለዚህ በዚህ ምርምር የተመረጡ የግእዝ ፍልስፍናዊ መጻሕፍትን መሰረት በማድረግ ከፍልስፍና ይዘት አንፃር ትርጉምና ትንታኔ ይቀርባል፡፡

የኢትዮጵያ የብራና መጻሕፍት በተለያዩ የእውቀት ዘርፎች የተሞሉ ናቸው፡፡ የባህላዊ ህክምና፣ የፍልስፍና፣ የፖለቲካ፣ የማኅበራዊ፣ የሥነ ከዋክብት፣ የአስተዳደር፣ የሥነ ሕንጻ፣ የህግ፣ የዘመን ቆጠራ፣ የሥነ መለኮት፣ የሥነ ጽሑፍ፣ የታሪክ፣ የሂሳብ እና ሌሎች መሰል የአዕምሮ ውጤቶችን በውስጣቸው አጭቀው የያዙ አያሌ ብራናዎች በአገራችን የተለያዩ መካናት፤ ገዳማትና ቤተ መዛግብት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ድርሳናት ይህን ያክል ጥልቀት ያላቸው ጥበባትን የያዙ ቢሆንም ቅሉ በዘርፉ ይህ ነው የሚባል ጥናት አልተደረገባቸውም፡፡ ጠቀሜታቸውም ተጠንቶ እውቀታቸው ተመዝብሮ ለማኅበረሰባዊ ጥቅም ውሏል ለማለት አያስደፍርም፡፡ በመሆኑም ይህንን ክፍተት በመመልከት በዘርፉ ምርምር ለማድረግ መግፍኤ ሆኖኗል፡፡ የምርምር ሙከራዎች ቢኖሩም ከዘርፉ ጥልቀትና ስፋት አንጻር በሚያረካ ደረጃ የቀረቡ አይደሉም፤ በተለይም የድርሳናቱ ፍልስፍናዊ ይዘት በሚገባ አልተመረመረም፡፡ በመሆኑም በዚህ ዘርፍ ያሉ ክፍተቶችን ለመሙላት ግብን ከማድረግ አንጻር ይህ ጥናት ቀርቧል፡፡ በርካታ በተለይ የውጭ ሃገር ምሁራን ኢትዮጵያ ውስጥ ብሎም አፍሪካ ውስጥ ፍልስፍና ስላለመኖሩ አበክረው ይከራከራሉ፡፡ የተጻፈም ይሁን ያልጽሑፍ የተላለፈ የፍልስፍና ጽንሰ ሃሳብ የለም በማለት ሲከራከሩ ይስተዋላል፡፡ በዚህ ጥናት ኢትዮጵያ ውስጥ ፍልስፍና አለ ወይ? የሚለውን ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ ጥረት ተደርጓል፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የሚነሳውን ጥያቄ ይመልስ ዘንድና የሚታየውን ክፍተት ለመሙላት ይህ ጥናት ተከናውኗል፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት በቀደምቱ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ፍልስፍናዊ ይዘት ነበረን? የኢትዮጵያ ፍልስፍና ምን መልክ አለው? ከግእዝ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ፍልስፍናዊ ይዘት ያላቸው ድርሳናት ነበሩ ወይ? ለፍልስፍና ጥናትስ የሚኖራቸው ፋይዳ ምንድነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡ የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ ጥንታዊ የብራና መዛግብት በፍልስፍና ረገድ ያላቸውን ፋይዳ መፈተሽና ለሃገራችን

በተጠቀሰው ዘርፍ የነበራቸውን አስተዋፅኦ መዳሰስ ነው፡፡ ጥናቱ ኢትዮጵያውያን በፍልስፍው ዘርፍ የነበራቸውን ቦታ የማሳየትና በግእዝ ሥነ ጽሑፍ ዙሪያ ግንዛቤ የመጨመር ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ በዚህ ጥናት የፍልስፍና ይዘት ያላቸው የመካከለኛው ዘመን መጻሕፍት ዓይነታዊ የጥናት ሥነ ዘዴን መሰረት በማድረግ ተተንትነዋል፡፡

## ፍልስፍና በግእዝ መጻሕፍት ውስጥ፤ ከፍልስፍና ዘርፎች አንጻር

### የኢትዮጵያ ፍልስፍናዊ ድርሳናት እና ፈላስፋዎች

በዚህ ክፍል የፍልስፍና ድርሳናት በሆኑት *ፊስአልጎስ፣ ዜና ስክንድስ ጠቢብ* እና *አንጋረ ፈላስፋ* እንዲሁም *ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብ* እና *ሐተታ ወልደሕይወት* ላይ በመመርኮዝ የግእዝ ውርስ ትርጉም የፍልስፍና ድርሳናት ላይና የኢትዮጵያውያኑ ፍልሱፋን ዘርዓ ያዕቆብና ወልደ ሕይወት ፍልስፍናዎች ላይ ትንታኔ ቀርቧል፡፡ በመሆኑም ድርሳናቱንና የኢትዮጵያውያኑን ፈላስፋዎች ሥራዎችና አተያይ በመቀጠል እንመለከታለን፡፡

#### *ፊስአልጎስ*

*ፊሳልጎስ* ስለተሰኘው የፍልስፍና ስራ በዝርዝር እንመለከታለን፡፡ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ የግሪክ፣ ሶርያ፣ ቅብጥ የመሰሉ የውጭ ቋንቋዎች ተጽዕኖ ትልቅ ነው፡፡ በተለይ ከአውሮጳ ልሳናት የጽርዕ ቋንቋና ባህል ተጽዕኖ በጉልህ ይታያል፡፡ ከአፍሪቃ ደግሞ ከቅብጥ ጋር የቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍ፣ ባህልና ሃይማኖት ጥብቅ ቁርኝትና የርስበርስ ተጽዕኖ በስፋት ይታያል፡፡ በተለይ ከመጀመሪያው እስከአራተኛው መቶ ክፍላተ ዘመናት ድረስ ከግሪክ ጋር የነበረው መስተጋብር ትልቅ ነበር፡፡ በዚህም የግሪክ አስተምህሮዎች በስፋት ይገኙ ዘንድ አስችሏል፡፡ ግሪክ ቀደም ብሎ በጥንታዊው ዘመን ለፍልስፍና፣ ከክርስትና መምጣት በኋላ ለክርስትና መበልጸግ ትልቅ ድርሻ ነበራት፡፡ ለዚህም ነው መንፈሳዊ/ክርስቲያናዊ እና ፍልስፍናዊ መጻሕፍት ከግሪክ ይተረጎሙ ዘንድ በር የተከፈተው፡፡

*ፊሳልጎስን* ከዚህ አውድ ጋር በተያያዘ እናገኘዋለን፡፡ *ፊሳልጎስ* የተደረሰው እስክንድሪያ (ግብጽ) ውስጥ ሲሆን ሃገሪቷም በግሪክ ግዛት ስር ነበረች፡፡ መጽሐፉ ሙሉ ለሙሉ ወጥ (ሃገራዊ) ስራ አለመሆኑን ልብ ይሏል፤ ከጽርዕ በውርስ የተተረጎመ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የደራሲው ስም ከርዕሱ ጋር በተመሳሳይ ፊሳልጎስ እንደሆነ ቢገለጽም፣ እንደ Sumner አባባል ከሆነ ግን ደራሲው በትክክል አይታወቅም፡፡ ቢሆንም የተለያዩ ቅዱሳን ሰዎች የመጽሐፉ ደራሲዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገመታሉ፤ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ፣ ቅዱስ ጴጥሮስ ሊቀ ጳጳስ

ዘእስክንድርያ፣ ቅዱስ አትናትዮስ ሊቀ ጳጳስ ዘእስክንድርያ፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እና ሌሎች የመጽሐፉ ደራሲነት ግምት የተሰጣቸው ናቸው (Sumner, 1998)፡፡ እንደ Sumner ግምት የመጽሐፉ ውርስ ትርጉም የተከናወነው በ5ኛው ክ/ዘመን መጀመሪያ ወይም አጋማሽ ሳይሆን አይቀረም፡፡ በግብጽ አገር በገዳመ አስቄጥስ ይኖሩ በነበሩ ኢትዮጵያዊ መነኮስ ወደ ግእዝ እንደተረጎሙት ይገመታል (1998)፡፡ በሌላ መልኩ መጽሐፉ በ2ኛው መ/ክ/ዘመን እንደተጻፈ የሚናገሩ እንዳሉ ሁሉ በ3ኛው መ/ክ/ዘመን መጨረሻ ወይም በ4ኛው መ/ክ/ዘመን መጀመሪያ ላይ መጻፉን የሚገምቱም አሉ፤ በተለይ Scott ከ3ኛው ክ/ዘመን በፊት የመጻፍ እድል እንደማይኖረው ያሰምርበታል (Scott, 1998)፡፡ የግእዙ ቅጽ ተርጓሚም በስም አይታወቅም[4]፡፡ ይህ ድርሰት በምሥራቃውያኑ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድም ዝነኛ ነው፡፡

መጽሐፉ ሃምሳ ሰባት የሚሆኑ ክፍሎች አሉት፡፡ አርባ ሁለቱ ስለእንስሳት፣ ሁለቱ ስለዕፅዋት፣ አራቱ ደግሞ ስለማዕድናት የሚያነሱ ይዘቶች አሉት፡፡ ስለሆነም ጭብጡ በእንስሳት፣ ዕፅዋትና ክቡር ድንጋዮች (ማዕድናት) ተፈጥሮአዊ ይዘት መሰረት በተምሳሌታዊ ውክልና ቀርቧል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ተምሳሌትና የሞራል እሴቶች ዋነኛ መለያዎች ናቸው፡፡ እንደ Cox (1983)፣ እንደ ፊስአልጎስ ከሃምሳ የሚልቁ እንግዴ ምዕራፎች ስብስብ ሲሆን፣ እያንዳንዱም የአንድን እንስሳ፣ ዕፅዋት ወይም ማዕድን ባህሪ ወይም "ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ" የሚናገር ነው፡፡ ለተለያዩ ዛፎች እና ዐለቶች የተሰጡ ጥቂት ታሪኮች ቢኖሩም፣ አብዛኛዎቹ ከእንስሳት፣ በተለይም ከዱር እንስሳት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ እነዚህ እንስሳት ስነመለኮታዊና ስነልቦናዊ እውነታዎችን የሚያመለክቱ ሆነው ታሪኮቹ ኤሊጎሪ፣ ስላቅና ተምሳሌታዊ እንዲሁም ሜታሞርፎሲስ ይዘትና አቀራረብ አላቸው፡፡ የምዕራፎቹ አወቃቀርም ትኩረት የሚስብ ነው፡፡ እንደየአስፈላጊነቱ እያንዳንዱ ምዕራፍ ወይም ክፍል ታሪኩ የሚነገርለት እንስሳ በተገለጸበት የብሉይ ኪዳን ጥቅስ ጅማሮውን ያደርጋል፤ ከዚያም የእንስሳቱ ተፈጥሯዊ ባህሪይ ይገለጻል፡፡ የእንስሳው ጥንተ-ተፈጥሮ ከክርስትና አውድ አንጻር ተምሳሌትነት ይዞ ይቀርባል፤ ከእንስሳው ታሪክ ጋር የሚዛመድ የሃዲ ኪዳን ጥቅስ ይወሰድና መንፈሳዊ ፋይዳ ባለው ምሳሌያዊ ውክልና ይብራራል፡፡

ጥቂት ማሳያዎችን ለናሙና ቀጥሎ እንመልከት፡

> በእንተ አሮድዮን…ወውእቱሰ ጠቢብ ፈድፋደ እምኲሉ አዕዋፍ ወኢያጸልል ኀበ መካናት ብዙኃት፤ አላ በአሐቲ ይሰክብ፤ ሶበ

[4] በኢትዮጵያ የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ልማድ የመጻሕፍቱ ደራስያን በአብዛኛው ስማቸውን አይገልጹም፡፡

ይቀርብ ኀበ ሰብእ ይከውን ዝልጉሰ፤ ወሶበ ቀርበ ያጠፍእ አልባሰ ሰብእ፤ ወአዲ ይሴሰይ ወይበልዕ ሥጋ ምውተ፤ አንትሙሂ ሕዝባውያን ወመነኮሳት ትጉሃን ኢታፍቅሩ ተፋልሶተ መካን ውስተ መካን፤ ባሕቱ ትኩንክሙ ምስካበ አሐቲ ቤ ክርስቲያን ቅድስት . . . ።

(ሮዳስ፣ 2010፣ገጽ 114)

ከላይ በተጠቀሰው ጥቅስ አሮድዮን ስለተባለ የወፍ ዝርያ በምሳሌነት ቀርቧል። አሮድዮን ከሁሉ ወፎች ጠቢብ እንደሆነ፣ በአንዲት ውስን ቦታ ይጸናል እንጂ በብዙ ቦታዎች እንደማይጠለል፤ ሆኖም ወደሰው በቀረበ ጊዜ እንደታመመ እንደሚሆን፣ የሰውን ልቦናም እንደሚያጠፋ፣ የሞተም እንደሚመገብ ገልጾ፤ በምሳሌውም ሕዝባውያንና ትጉሃን መነኮሳት ከቦታቦታ መዘዋወርን መውደድ እንደሌለባቸው፤ መጠጊያቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ብቻ መሆን እንዳለባት ይናገራል። አሮድዮን ወፍ ከሚኖርበት አንድ ውስን ቦታ ተለይቶ ብዙ ቦታዎችን ከዞረ መልካም እንደማይሆን ሁሉ አንድ መነኮስም ከበዓቱ ከተለየ ወደከተማና ሕዝብ ወደሚበዛበት አካባቢዎች መንቀሳቀስ ካበዛ በመንፈሳዊ ልዕልናውና ክብሩ ላይ ውድቀት እንደሚከተል ሲያጠቅ ነው። በፊስአልጎስ ውስጥ የተጠቀሱ አንዳንድ የአውሬና የአእዋፍ ዝርያዎች መኖራቸውን እንኳ ብዙም የማይታወቁ ናቸው፤

በእንተ እብነ አድማስ ጽኑዕ ዘ፪ ፍጥረቱ፤ ባህቱ ኢኮነ ወኢይትከሀል ሶበ ይዘብጥዎ በሰፌልያ ፪ወ፲ቱ ነሀብት፤ ወኢሳትኒ ኢይክል ፈቲኖቶ፤ ወጼና ጢስ ይለክፎ እምብዝኃ ላህቡ፤ ወለእመ ተደመረ ውስተ ሕንጻ ቤት ኢይክል ጋኔን ርኩስ ከመ ይባእ፤ ምሳ አድማስሰ ኮነ በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ወእመ ክርስቶስ ውስተ ልብከ ኢይክል ቀሪበ ኀቤከ ኩሉ ከንቱ፤ ዓዲ ከመ ይዘብጥዎ ለአድማስ፤ ከማሁ ዘበጥዎ ለእግዚእነ ኢየሱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሠገራተ ሰጺራ ወሕዝበ ሐና ወቀያፋ፤ ወጠብለልዎ ገጾ በሰበን እንዘ ይኮርዕዎ ርእሶ፤ ወይብልዎ ተነበይ ለነ ክርስቶስ መኑ ኮርዐከ፤ ወባዕዳንሂ ብዙኃን ይጸርፉ ላዕሌሁ፤ወዘንተ ኩሎ ተዐገሠ፤ በከመ አድማስ ይትዌከፍ ዝብጠተ ከመ ይቤዝወነ በጥብሐ ሥጋሁ ቅዱስ ወበክዕወተ ደሙ ክቡር ነባቢ።

(ሮዳስ፣ 2010፣ ገጽ 102-104)

ከላይ የቀረበው ጥቅስ አድማስ ድንጋይ ስለተባለ የከበረ ድንጋይ የቀረበ ተምሳሌታዊ ገለጻ ነው። አድማስ ድንጋይ ዐሥር ሺህ ዐሥር ጊዜ በመዶሻ ቢመቱት፣ በእሳት ሊያቀልጡት የማይቻል፣ በሕንጻ ቤተ

ክርስቲያን ቢያገቡት ጋኔን ይገባ ዘንድ አይቻለውም፡፡ የዚህ ድንጋይ ምሳሌነት ኢየሱስ ክርስቶስ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ክርስቶስ በልቡ ውስጥ ላለ ሰው ከንቱ ነገር ወደእርሱ ሊቀርብ አይችልም፡፡ ክርስቶስን ወታደሮች፣ የሐናና ቀያፋ ወገኖች መቱት፤ ፊቱን በሻሽ ጠቅልለው ራሱን በዘንግ እየመቱ ትንቢት ተናገርልን ራስህን ማን መታህ እያሉ፣ ብዙዎችም በእርሱ ላይ ይዘባበቱ ነበር፡፡ አድማስ ድንጋይ መመታትን እንደተቀበለ ሁሉ ክርስስም ተንገላትቶ ስቃይን ተቀብሎ በሥጋው መሠዋትና ነባቢ በሆነ ክቡር ደሙ መፍሰስ የሰውን ዘር መቤዠቱን ያጠይቃል፡፡ አንድም የአድማስ ጥንካሬ የኢየሱስን የባህርይ አምላክነትና ሁሉን ቻይነት ሲያሳይ፤ ኃያል የሆነው ድንጋይ አድማስ በመዶሻም በእሳትም መፈተኑ፣ ኃያል አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ለማዳ የተቀበለውን መከራ ወክሎ ይቀርባል፡፡

በመጽሐፉ ውስጥ በምሳሌነት የቀረቡ እንስሳት፣ ዕፅዋትና የከበሩ ድንጋዮች የሞራል እሴቶች ተምሳሌታዊ አስተማሪነት አላቸው፡፡ ብርጋና ወፍ፣ ሐለስትዮ፣ ቋርምስ ዛፍ፣ ሆባይ፣ ዝኆን የአድማስ ድንጋይ፣ ፌቆ፣ መንጢጥ ወፍ፣ ሳቤሳ፣ ጽርያኖስ ወፍ፣ መጎንጢስ ድንጋይ፣ ጳረቦሎስ ድንጋዮች፣ እንደራጳስ አውሬ፣ ቀይ ርግብ፣ ከለደን ወፍ፣ ኤጺስክዮ ዛፍ፣ ዋሊያ፣ ዋስ፣ ኢክሞን፣ ኤኖድርዶን፣ መንቆሪጦስ (ባለአንድ ቀንድ እንስሳ)፣ ቀስጦርዮስ አውሬ፣ እና መሰል ፍጥረቶች ሥነ ባሕርይ ውክልና ቀርቧል፡፡ ግብረ ገባዊ እሴቶችና ነገረ ሰናይት፤ ክርስቲያናዊ አስተምህሮ በድርሳኑ ውስጥ ግዘፍ ይነሳሉ፡፡ ምንም እንኳ ሰውን ማዕከል ያደረገ ፍልስፍናዊ አቀራረቡም በሃይማኖታዊ መነጽር ብቻ ሊታይ እንደማይችል ያጠይቃል፡፡ ተፈጥሮን ተምሳሌትነት በመጠቀም ክርስትናዊ ትምህርትን የሞራል፣ ግብረ ገብና ነገረ ሃይማኖትን የሚያቀርብ ነው፡፡ *ፍስአልጎስ* የእንስሳት፣ የእፅዋት እና የድንጋዮችን አስደናቂ ባህሪያት ገላጭ በሆነ አቀራረብ እያንዳንዳቸውን ክርስቲያናዊ ትርጉምና ውክልና ሰጥቶ ያቀርባቸዋል፡፡ ለክርስትና ነገረ ኃይማኖት ትምህርት *ፍስአልጎስ* ምሳሌዎችን/ተምሳሌቶችን በማበርከት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡ የመጽሐፉ መተርጎም ለኢትዮጵያ የፍልስፍና አስተሳሰብ ትልቅ ተጽዕኖ አለው፤ ይዘቱም ከፍልስፍናና ሥነ ጽሑፍ ባሻገር ለሥነ ሕይወትና ሥነ ምድር ምርምር በር ከፋችም ነው፡፡

## *ዜና ስክንድስ* ጠቢብ

በኢትዮጵያ ፍልስፍና ጥናት የሚታወቀው ሁለተኛው መጽሐፍ *የስክንድስ ሕይወትና አስተምህሮቱ* ወይም *ዜና ስከንድስ* ይባላል፡፡ ስክንድስ በጥንታዊው ዘመን የነበረ የግሪክ ፈላስፋ ነው፡፡ በመጽሐፉ ያስፈረው እናትና አባቱ ፍልስፍና እንዲያጠና ወደ አቴንስ ከላኩት በኋላ የመረመረውን እውነታ ነው በመጽሐፉ የገለጸው፡፡ የኢትዮጵያው

መጽሐፈ ስክንድስ ቅጽ ከዐረብኛ የተተረጎመ ሲሆን ትርጉሙ የተከናወነው በዘመነ ዘርዓ ያዕቆብ ነው፡፡ ስክንድስ የኢትዮጵያ ፍልስፍና ማጥኛ የሆነ የግእዝ ፍልስፍና ድርሳን ነው፡፡ የስክንድስ ሕይወትና አባባሎቹ የፍልስፍ መጽሐፍ በዘመነ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ወደግእዝ እንደተተረጎመ የሚታወቀው ሲሆን *ዜና ስክንድስ* በመባልም ይታወቃል፡፡ ጠቢቡ ስክንድስ በክርስትና የመጀመሪያዎቹ ዘመናት የነበረ የግሪክ ፈላስፋ ነው (Sumner, 1981፤አማኑኤል 2011)፡፡ ወላጆቹ ፍልስፍናን እንዲያጠና ወደ አቴንስ ልከውት የተመራመረውን ነገር ነው መጽሐፉ የሚገልጥልን፡፡ ይህ መጽሐፍ በሁለት የምዕራብ ቋንቋዎች (ላቲንና ግሪክ) እና በሦስት የምሥራቅ ቋንቋዎች (ሲርያክ፣ ዓረብኛና ግእዝ) ይገኛል፡፡

*ዜና ስክንድስ* ሶስት ክፍሎች ሲኖሩት የመጀመሪያው ስለስክንድስ ሕይወት ሲያትት፣ ሁለተኛው 55 ጥያቄዎችንና ፍልስፍናዊ መልሶቻቸውን ይይዛል፣ ሦስተኛው ክፍል ደግሞ 108 የፍልስፍና ጥያቄዎችን እያነሣ መልስ ይሰጣል፡፡ ስክንድስ የእናቱን ሞት ተከተሎ ለምላሱ ዝምታን ከመረጠ፣ ሕይወቱን በዝምታ ለማሳለፍ ከወሰነ በኋላ በአርምሞ መፈላሰፍ ያዘ፡፡ ከተለያዩ የፍልስፍና ዘርፎች ዲበ አካላዊነት፣ ሥነ እውቀት፣ ሥነ ውበት፣ ሥነ ምግባር፣ ሥነ አመክንዮ፣ወዘተ አንጻር ይጠናል፡፡ ከታች ዘርዓ ያዕቆብና ወልደሕይወት የእንስታዊነት ፍልስፍና አራማጆች እንደነበሩ ተብራርቷል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ጠቢብ ስክንድስም ስለሴትነት አዎንታዊ እይታ እንደነበረው ቀጥሎ በቀረበው ጥቅስ መገንዘብ እንችላለን፡፡ ስክንድስ የፍልስፍና ት/ቤት በነበረበት ጊዜ ስለሴት ያልተገባ ነገር ተጽፎ ተመለከተ፡፡ በመምህራኑ ስለሴቶች ተጽፎ ያስተዋለው ቃል፤ “ሴቶችም ሁሉ አመንዝራዎች ናቸው” የሚል ነበር፡፡ ይህን ባየ ጊዜ ፈላስፋው ስክንድስ ከልቡ ቁጣን ተቆጣ፡፡ የመጀመሪያ መምህሩንም እንዲህ ሲል ተቃወመው፤ “ሴቶች ምን አደረጉት፣ ይህን ጎደሎ ነገር የተናገረ ከሴት ተወለደውን ሁሉ የሚያዋርድ ነው፤ ወንድ የማያውቁ ሴቶች ጥበበኞች ናቸው እንጂ ሁሉም ሴቶች አመንዝራዎች …” (አማኑኤል፣ 2011፣ገጽ 56) ፡፡ በዚህም በመነሳሳት ሴትነትን በተመለከተ ጥያቄዎችን መጠየቅ መመርመርም ጀመረ፤ ስለሴት የተጻፉ ነገሮችንም መረመረ፣ እናቱንም ጨምሮ ሴቶችን መፈተን እንዳለበት አሰበ፡፡ ስክንድስ የሴትን ክብር ዝቅ በሚያደርጉ አስተሳሰቦችን አይጋራ አንጂ አመንዝራነትን አስመልክቶ የገዛ እናቱን እስኪፈትን ድረስ የሄደበት ምርምር ሴቶችን ከወንዶች ለይቶ የመታመን ግዴታን የሚያሸክም ነው፤ ወንዶችም በዚያው ትይዩ በአመንዝራነትን ድርጊት ይተቹ ዘንድ ይገባልና፡፡

***አንጋረ ፈላስፋ***

*አንጋረ ፈላስፋ* (*“የፈላስፋዎች አነጋገር”*) በሚል ርእስ በሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ በ1953 ዓ.ም ከግእዙ ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉሟል፡፡ ተርጓሚው በመቅድሙ እንደገለጸው መጽሐፉ *“ከክርስቶስ ልደት በፊት በየዘመናቸው የተነሱ የግሪክ (የሌሎችም አገር) ፈላስፋዎችና እንዲሁም ከክርስቶስ ልደት በኋላ የተነሱ መንፈሳውያን ሊቃውንት ከተናገሩዋቸው ምርጥ ምርጥ ቃላት ተውጣጥቶ በቀድሞዎቹ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ትጋት የጽርዑን ከጽርዕ የዓረብኛውን ከዓረብኛ ቋንቋዎች ወደግእዝ የተገለበጠ ነው”* (ሞገስ፣ 1953፣ገጽ 6)፡፡ በ*አንጋረ ፈላስፋ* የተለያዩ ፈላስፋዎች አስተሳሰቦችና አባባሎች ተዘርዝረው ቀርበዋል፡፡ አባባሎችን ሲያቀርብ የፈላስፋዎችን ስም እየጠራ “እገሌ የተባለው ፈላስፋ እንዲህ አለ…” ሲል፣ በስም ያልጠቀሳቸውን ፈላስፋዎች ንግግር ደግሞ “አንድ ፈላስፋ እንዲህ አለ፣ ፈላስፋ እንዲህ አለ…” እያለ ያቀርባል፡፡ የቅድመ እና ድኅረ ክርስትና ፈላስፎችን ስራዎች የያዘ ነው፡፡

በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት አባባሎች የተለያዩ የፍልስፍና ይዘትና እሳቤዎችን ያንጸባርቃሉ፡፡ ስለ ሕይወት፣ ስለ ሞት፣ ስለ ነፍስ፣ ስለ እውቀት፣ ስለ ግብረ ገብ/ምግባር፣ ስለኃጢአት፣ ስለ እውነት እና ሌሎች ጽንሰ ሃሳቦች የፈላስፋዎች እይታዎች ተቀምጠዋል፡፡ ለምሳሌ ያክል የሚከተለውን ቅንጭብ እንመልከት፡- “*አንድ ፈላስፋ ከአእምሮ የሚበልጥ ምንም አይገኝም አለ፡፡ ነገሥታቱ በሕዝብ ላይ ይፈርዳሉ፤ እንደዚሁም አዋቂዎቹ በነገሥታቱ ላይ ይፈርዳሉና*” (ሞገስ፣ 1953፣ገጽ10)፡፡ *አዕምሮ ወይም ዕውቀት የነገሮች ሁሉ እናት ስለመሆኗ ነው የተናገረው፡፡ ዕውቀት ያለው ሰው ከሁሉም እንደሚልቅ ያሳየናል፡፡ በሕዝብ ላይ በማናለብኝነት የሚፈርዱ/ፍርድን የሚገመድሉ ነገሥታት ላይ ዕውቀት ገንዘባቸው የሆነ ጠቢባን/አዋቂዎች ሊፈርዱባቸው፣ ሊገስጹአቸውና ሊተቿቸው እንደሚችሉ ያስረዳል፡፡ ሞት ለሃብታሞች እሬት ለድሆች ደግሞ ጣፋጭ እንደሆነች ዲዮጋንስ ያምናል፡፡ ሞት እንደምንድር ናት?* ብለው ቢጠይቁት በዝናና በድሎት ለመኖር ለሚቋምጡት ባለጸጎች እንደምታስደነግጥ ነገር ግን ለመኖር ብዙም የሚያጓጓ የሕይወት ዘይቤም የሕይወት ጥፍጥናም ለሌላቸው ድሆች ግን ሞት ጉዳያቸው እንዳልሆነ አልፎም እንደምትናፍቃቸው ነው ዲዮጋንስ የተናገረው፡፡ አባባሉ እንዲህ ይነበባል፡- “*ዲዮጋንስ ሞት እንደምንድር ናት? ቢሉት ሞትስ ባለጸጎችን የምታስደነግጣቸው ድሆችን የምትናፍቃቸው ናት አለ፡፡*” (ሞገስ፣1953፣ገጽ 14) ፡፡

ፒታጎረስ ስለ ነፍስና *ሥጋ* እንዲህ ይላል፡- “*ፈላስፋው ፒታጎሮስ ነፍስ ሥጋን ካላሸነፈቻት እንግዲህ ሥጋ ለነፍስ መቃብር ሆነች ማለት ነው ብሏል*”፡፡ (ሞገስ፣ 1953፣ገጽ 29)፡፡ *ረቂቋ ነፍስ ግዘፍ ያለውን ሥጋ*

ድል የመንሳት መንፈሳዊ ኃይል ይኖራታል ማለት ነው፡፡ ነፍስ ሥጋን ማሸነፍ አለባት፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ሥጋ ለነፍስ መቃብሯ ትሆናለች፡፡ ግዙፉ ሥጋን ኀጢአት ነግስበታለች፡፡ ረቂቋ ነፍስ ግን መንፈሳዊት ናት፤ የረቀቀውንና መልካሙን ትፈጽማለች፡፡ ሠናይትን ለማድረግ በሥጋ ላይ የበላይነትን መጎናጸፍ አለባት፡፡ የሥጋ ሥጋ ካየለ ክፋት ይነግሥና ሰናይት ትከሽፋለች፡፡ ወዲያውም ፒታጎረስ እንዳለው ሥጋ ለነፍስ መጥፊያዋ ወይም መቀበሪያዋ ሆነች ማለት ነው፡፡ የጥንት ዘመን የአውሮፓ ነገሥታት ጠቢባንን እንደማይወዱ ነገራል፡፡ ብልህ ንጉሥ ካላጋጠመ በቀር አዋቂዎችን ቤተ መንግሥት አቅርቦ የሚጠቀምባቸው አይኖርም፡፡ ጠቢባን ግልብ እና አምባገነን ነገሥታትን ይቃወማሉ፡፡ በአመክንዮ ይተቻሉ፡፡ ለዚህም በምላሹ ነገሥታቱ ከፉኛ ሲቀጧቸው ኖረዋል፡፡ ፈላስፋዎቹም በዋዛ አይተዋቸውም፡፡ የመጨረሻዋን ሞት እስኪጎነጪት ድረስ ይፋጠጣሉ፡፡ በአንጋረ ፈላስፋ ላይ ስሙ ያልተጠቀሰው ፈላስፋ እንዲህ አለ፡- “ከፈላስፎች አንዱ ንጉሥ አይወድህም ቢሉት አዎን ንጉሥ የሚበልጠውን አይወድምና ነው አላቸው” (ሞገስ፣ 1953፣ገጽ 32)፡፡ ንጉሡ በጡንቻው፣ በብረት ብዛት ማንንም ያሸንፋል፤ ረግጦ ይገዛል፡፡ ፈላስፋ ጠቢብም በእውቀቱ ብዛት ይበልጠዋል፤ ስለዚህም ጠቢቡ ንጉሥ ቢጠላኝ ስለምበልጠው ነው አለ፡፡

“ሶቅራጥስ አንዲት ሴት ደርሳ አረግ! መልክህ ምንኛ ክፉ ነው ብትለው በዛገው መነጽርሽ ብታይኝ ነውኮ ሲል መለሰላት”፡፡ (ሞገስ፣ 1953፣ገጽ 44)፡፡ “ነገሮች ሁሉ አንጻራዊ” እይታ አላቸው እንደሚባለው፤ አስተሳሰብ/አመለካከት እንደየተመልካቹ የተወሰነ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ውበት በተመልካቹ የማየት መጠን ወይም ግለሰባዊ ምልከታ አንጻራዊ ሆኖ ቀርቧል፡፡ አንድም ውጫዊውን ውበቱን እንጂ ውስጣዊውን መመልከት አልቻለችም እንደማለት ነው፡፡ ሰባራ መነጽር (ወይም ንጹህ ያልሆነ፣ የዛገው) ትክክለኛውን ገጽታ አያሳይም ሲል ነው፡፡ የውጭ ውበቱን አይታ መልከ ጥፉ ብትለው ውስጣዊ ውበቱ ወይም እውቀቱ ግን የመጠቀ መሆኑን መመልከት እንዳልቻለች ሲነግራት ነው፡፡ “አርስጣጣሊስ ለሁሉም ነገር የተለየ የየራሱ ሥራ አለው፤ ነገር ግን የልብ ስራው የተወደደና የተመረጠ መሆን ነው አለ” (ሞገስ፡ 1953፣ ገጽ 48)፡፡ ወዳጅ ከወዳጁ ከጠላት ጋር ስምሙ ከሆነ በሌላ መልኩ ከልብ ወዳጅ አልነበረም ማለት ነው፤ ወይም በጎን ከጠላት ጋር እያበረ ነው፡፡ ይህኛው በአንጋረ ፈላስፋ ላይ የቀረበ ጠቢብ “ፈላስፋ እንዲህ አለ፤ ወዳጅህ ለጠላቶችህ ከታዘዘ እንግዲህ አንተን ለመጣላት እንዳበረላቸው እወቅ” (ሞገስ፣ 1953፣ ገጽ 54)፤ እያለ ሥነ አመክንዮአዊ ሙግት ያቀርባል፡፡ አንጋረ ፈላስፋ ወይም መጽሐፈ ፈላስፋ ጠቢባን የበርካታ የግሪክ እና ሌሎች አገሮች ፈላስፋዎችን አስተሳሰብ የያዘ መጽሐፍ ነው፡ ፡ የሶቅራጥስ፣ አፍላጦን፣ አርስጣጣሊስ፣ ዲዮጋንስ፣ አብራጥ፣

ሀርሙስ፣ ሶልስ፣ አርስጡላ፣ፒታጎሮስ፣ ጋሊኖስ፣ ድምቅራስ፣ እስክንድር፣ በርዘመሃል፣ ሕኔን፣ ልቅማን፣ እና ሌሎች ፈላስፋዎች አባባሎችና አስተሳሰቦች ሰፍረው ይገኛሉ፡፡

## የዘርዓ ያዕቆብ ፍልስፍና፤ *ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብ*[5]

ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ በክርስትና ስሙ ዘርዓ ያዕቆብ (ወርቄ) በ16ኛው ክ/ዘመን (1592 ዓ.ም)[6] በአክሱም በካህናት አገር ከገበሬ ቤተሰብ መወለዱን የሕይወት ታሪኩንም ባሰፈረበት የፍልስፍና ጽሑፋዊ ስራው ከትቦታል፡፡ የዘርዓ ያዕቆብ በጽሑፍ የቀረበ የፍልስፍና *ሥራ ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብ* ይሰኛል፡፡ ሃተታው የተለያዩ የፍልስፍና እሳቤዎችንና አመክኖአዊ (rational) አተያዮችን የያዘ ነው፡፡ ከልዩ ልዩ የፍልስፍና ዘርፎች አንጻር ሊጠና ይችላል፡፡ የዘርዓ ያዕቆብ ፍልስፍና ከሥነ እውቀት (Epistemology) አንጻር መዳኘት ይችላል፡፡ ሥነ እውቀት ስለ እውቀት የሚያጠና ኃልዮት ነው፡፡ እውቀት መሰረቷ ምንድነው? ከወዴትስ ተገኘች? የመሰሉ የእውቀትን ስረ መሰረት የሚያስሱ ጥያቄዎችን እያነሳ ይመረምራል፡፡ እንደአመክንዮ መር (Rationalist) ፈላስፋዎች፣ የእውቀት ምንጭ ምክንያት (Reason) ነው፡፡ እንደEmpiricist ፈላስፋዎች ደግሞ የእውቀት ምንጩ ልምድ (Experience) ነው፤ የስሜት ልምድ (Sense experience):: ዘርዓ ያዕቆብ እውቀትን በምክንያት ሊያገኛት ይዋትታል፤ ምክንያትን (Reason) እውቀትን ለማግኘት ተጠቅሞበታል፡፡

ዘርዓ ያዕቆብ በእግዚአብሔር የሚያምን ፈላስፋ ነው፡፡ ምንም እንኳ በእግዚአብሔር ህላዌም መግቦት እምነት ያለው ቢሆንም እምነቱ ግን በምክንያት የተረገጠ ነው፡፡ የእውቀት ምንጭ እግዚአብሔር እንደሆነ ያምናል፡፡ አዕምሮውን በመጠቀም የሰው ልጅ ሁነትን በመመርመር ከእውነታው ዘንድ መድረስ አለበት ብሎ ያምናል፡፡ ዘርዓ ያዕቆብ የጥበብ ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር ነው ይላል፡፡ ፈጣሪ፣ ሁሉን ዐወቅ፣ ሁሉን ቻይ፣ ጠባቂ፡፡ "ሁሉን በፈጠረ መጀመሪያና መጨረሻ በሆነ ሁሉን በያዘና የሕይወትና የጥበብ ሁሉ ምንጭ በሆነ እግዚአብሔር…" (ጌታቸው፣ 2006፣ ገጽ 14) ይላል፡፡ የፈላስፋ ዘርዓ ያዕቆብ ሐተታ ከሥነ እውነታ (Metaphysics) የፍልስፍና ዘርፍ አንጻር ሊታይ ይችላል፡፡ ሥነ እውነታ በሰፊ አውድ ትርጓሜው የእውነታ (reality) ጥናት ማለት ነው፡፡ ዘርፉ በውስጡ ጥልቅ ይዘትና ጥያቄዎች ቢኖሩትም በዋናነት ግን እውነታ (reality) ምንድነው? ነጠላ/አንድ ነው ወይስ

---

[5] የዘርዓ ያዕቆብ ሃሳብ የተወሰደው፤ ጌታቸው ኃይሌ *ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብ በመባል የሚታወቀው የወርቄ ታሪክ*፤ ብሎ ከተረጎመው ነው፡፡

[6] ዘርዓ ያዕቆብ በ1685 ዓ.ም እንዳረፈ ይታመናል፡፡

ጥቅል/ብዙ? እውነት ምንድንነች? እያለ የሚጠይቅና የእውነትን ምንነት የሚያስስ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ወደ መንፈሳዊው ወይም ልዕለ ተፈጥሮ የሆነውን እውነታ ማሰሱ ላይ ያደላል፡፡ ዘርዓ ያዕቆብ በእግዚአብሔር ህልውና የሚያምን (አማኔ ልዕለ ተፈጥሮ) ፈላስፋ ነው፡፡ ዘርዓ ያዕቆብ የእግዚአብሔርን ህልው መሆን ያስረገጠበት የራሱ የሆነ መንገድ አለው፡ ፡ "ሜታፊዚካዊ" ጥያቄዎችን እያነሳ ይሞግታል፡፡

አማንያን "የኔ ሃይማኖት ትክክል ነው፣ የሌላው ግን ትክክል አይደለም" (ጌታቸው፣ 2006፣ ገጽ 34)፤ እያሉ ስለምን እርስበርስ ይወጋገዛሉ ብሎ ይሞግታል፡፡ የራሳቸውን እውነት የሌላውን ስህተት ስለምን ያደርጋሉ በማለት ይተቻል፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ ይገለጽለት ዘንድ ከእንደዚህ አይነት እሰጣገባ የሚርቅበትን መንገድ አምላኩን ይለምነዋል፤ ልሒቅ እና ምክንያታዊ ያደርገው ዘንድ አምላኩን ይጠይቃል፡፡ ዘርአ ያዕቆብ "ሜታፊዚካዊ" በሆነ መንገድ የእግዚአብሔርን ሕልውና ይጠይቃል፡፡ እንዲህ እያለ የልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይልን ህልው መሆን ይመረምራል፡፡ እውነትን መርምሮ በማረጋገጥ ነው የሚያምነው፡፡ ዘርዓያዕቆብ ስለእንስታዊነት አዎንታዊ አመለካከት ሰንዝሯል፡፡ "ወንድና ሴት በጋብቻ በአንድ ስጋና በአንድ ንብረት ትክክል ናቸው እና ጌታና ባሪያ ልንላቸው አይገባም" (ዳንኤል፣ 2007፣ ገጽ 53) እያለ ይከራከራል፡፡ ይህ አመለካከት ከእንስታዊነት ፍልስፍና አንጻር አስደናቂ እንደሆነ በተለይ የዘመኑን አውድ ተመልክተን እንገነዘባለን፤

> ይህችም ሂሩት ሚስቴ ሆነችና በጣም ወደደችኝ፡፡ በጌታዬ ሃብቱ ቤት የተናቀች ነበረችና፤ ቤተሰቦቿም ዘወትር ያሳዝኗት ስለነበሩ ዛሬ በጣም ተደሰተች፡፡ እኔም ስለወደደችኝ በተቻለኝ ሁሉ እንዳስደስታት በልቤ ወሰንኩ፡፡.... ከሚስቴ ጋር በፍቅር ነበርኩ፡፡ እኔ እየጻፍኩ የጌታዬን ሃብቱን ልጆች ሳስተምር እርሷም ቀንና ሌሊት ትፈትል ነበር...
>
> (ዳንኤል፣ 2007፣ ፣ ገጽ 41)

በጥቅሱ ላይ ሴቷን ከእርሱ ጋር እኩል እያደረገ ነው የገለጻት፡፡ ስለወደደችው እንዲሁ ተቀብሎ አልተዋትም፤ ይልቁንም እሱ መልሶ አብልጦ እንዴት እንደሚወዳት ይጨነቅ ነበር፡፡ መዋደድ ከሁለቱም ወገን መምጣት እንዳለበት ያምናል፡፡ በንብረት ክፍፍልም እኩል ነበሩ፡፡ የሚያገኙትን ሁሉ እኩል እንዳገኙና እኩል የንብረት ተካፋይነት መብት እንዳላቸው ይናገራል፡፡ በስራ ክፍፍልም እንደዚሁ፡፡ እርሱ በመጻፍና በማስተማር ገቢ ያገኛል፤ እሷ በበኩሏ ተግታ በመፍተል ገቢ ታስገኛለች (ዳዊት፣ 2011)፡፡ የዘርዓያዕቆብ ፍልስፍና ከተለያዩ የፍልስፍና ዘርፎች ዲበአካላዊነት፣ *ሥነ* እውቀት፣ *ሥነ* ውበት፣ *ሥነ* ምግባር፣ *ሥነ* አመክንዮ አንጻር ይጠናል፡፡ *ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብ* ኢትዮጵያ ፍልስፍና

ማጥኛ የፍልስፍና ድርሳን ነው። ዘርዓ ያዕቆብ የኢትዮጵያ ፍልስፍና ጀማሪ ነው። በሁሉም የፍልስፍና ዘርፎች አንጻር ይቀርባል። ከነሬኔ ዴካርት ዘመናዊ ፍልስፍና ጋር ፍልፍናውን የሚያነጻጽሩ አሉ። የኢትዮጵያን ዘመናዊ ፍልስፍና ጅማሮው ከዘርዓ ያዕቆብ ጋር የተያያዘ መሆኑን ያጠይቋል።

## የወልደ ሕይወት ፍልስፍና፤ *ሐተታ ወልደ ሕይወት*[7]

ፈላስፋው ወልደ ሕይወት የዘርዓ ያዕቆብ ደቀ መዝሙር እንደመሆኑ ፍልስፍናው ከመምህሩ ጋር በአብዛኛው ተመሳሳይነት አለው። ወልደ ሕይወት የዘርአ ያዕቆብን አስተምህሮ የተከተለ ነው። ከሥነ እውቀት (epistemology) የፍልስፍና ዘርፍ አንጻር ስናየው ወልደ ሕይወት አመክንዮ መር (rationalist) ፈላስፋ ነው። እንደዘርዓ ያዕቆብ ሁሉ የእውቀት ምንጭን ምክንያት (reason) እንደሆነ አድርጎ የሚመረምር ነው። እውቀትን በምክንያት ለማግኘት ይመረምራል። እውቀትን ለማግኘት ምክንያትንተ ጠቅሟል። እንደ መምህሩ ሁሉ ወልደ ሕይወትም የእውቀት ምንጭ እግዚአብሔር ነው ብሎ ያምናል። ይህንንም በምክንያት ይፈትናል። ወልደ ሕይወት አንድን ሁነት በደፈናው ከመቀበል በፊት ምክንያትን ያስቀድማል። በእምነት ከማስረገጥ በፊትም ምክንያትን ያስቀድማል፤ ከእምነት በፊት በአንክሮ መመርመር። ያለምርምር ወይም ጥያቄ የሚደረግን እምነት በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ እንዳልሆነ ወልደ ሕይወት ያምናል፣ ምክንያታዊ ለሆነው የሰው ልጅም ሳይጠይቅ እንዲሁ መቀበል ለባህርይው አይመጥንም ባይ ነው። የወልደ ሕይወት ፍልስፍና ከዘርዓ ያዕቆብ የቀጠለ ዘመናዊ ፍልስፍና ነው። የዘርዓ ያዕቆብን አስተምህሮ በሚገባ አስፋፍቶ አስቀጥሎታል። በፍልስፍና ዘርፎች አንጻር ሲዳኝ ወልደ ሕይወት የረቀቀ ፍልስፍና አለው። በ*ሐተታ ወልደ ሕይወት* ላይ ይህን እንመለከታለን፤

> … በልቦናህ ም ዓይን ወደእርሱ ተመልከት። ፈጣሪህ የሚያሳይህን የምርምር ብርሃን ተመልከት። የሚያስተምሩህ ትምህርታቸውን በተውክ ጊዜ ፈጣሪን ካደ እያሉ የሚሰድቡህን ቃላቸውን አትስማ እነርሱ ፈጣሪያቸውን አላወቁትም፣ በእነርሱ ዘንድ ጥበብ የለም። አንተ ግን አስተምህሮታቸውን ራስህ ሳትመረምረውና እውነትን ከሃሰት ለይተህ ካልሆነ በቀር ሰዎች የሚያስተምሩህን ምንም አትመን። ምክንያቱም ሰዎች ሊዋሹ ችላሉ… እንደዚሁም ሳትመረምራቸው በመጻሕፍት የተጻፉትንም

[7] በማጣቀሻነት ጥቅም ላይ የዋለው የዳንኤል ወርቁ (2007፣ 4ኛእትም)። *ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብ እና ሐተታ ዘወልደ ሕይወት*፣ መጽሐፍ ነው።

> አትመን። መጻሕፍትም በሀሰት ሊፅፉ በሚችሉ ሰዎች የተፃፉ ናቸውና። አንተ ግን መጻሕፍትን ከመረመርካቸው እግዚአብሔር እውነትን እንድንፈልግት ከሰጠን ከልቦናችን ጋር የማይስማማ ክፉ ጥበብ ታገኝባቸዋለህ።
>
> (ዳንኤል፣ 2007፣ ገጽ 49)

እንደወልደ ሕይወት እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ልቦና/አእምሮን ይመረምርበት ዘንድ ፈጥሯል። ራሱን እግዚአብሔርን ለማወቅም የሰው ልጅ ሰዎች ዌም መምህራን ከሚነግሩት አሊያም ሰዎች ከልቦናቸው አንቅተው ከሚጽፉት ይልቅ በራሱ ልቦና/ሕሊና መርምሮ እውነቱ ላይ መድረስ እንዳለበት ያስገነዝባል። ለእውቀትም ሆነ አንዳች እውነታ ላይ ለመድረስ መነሻ ምንጩ በምክንያት መመርመር መሆኑን ያምናል።

በሌላ መልኩ አሰላሳዮቹ ዘርዓ ያዕቆብ እና ወልደ ሕይወት የጻፏቸውን የፍልስፍና ሐተታዎች ላይ የ"ሴት"ና "ሴትነት"ን ውክልናን እንስታዊነትን (feminism) እንደንድፈ-ሃሳባዊ መቀንበቢያ በመጠቀም መተንተን ይቻላል። የእንስታዊነት ንድፈ-ሐሳብ የቅርብ ጊዜ ንቅናቄ ሲሆን በሴቶች የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አቅም መጎልበትና እኩላዊ ሱታፌ ላይ ያተኩራል። ሴቶች ተነጥለው ዝቅ የሚደረጉባቸውን፣ የሚገለሉባቸውንና የሚበዘበዙባቸውን መንገዶች በመለየት ይቃወማሉ። በሃገራችን የነበረን የሴትነት አረዳድ ምን ይዞታና ታሪካዊ ዳራ እንዳለው በአገራችን ፈላስፎች አመክንዮ መሰረት ማየት ሲሆን በተለይ ዓለም-ዓቀፉ ማኅበረሰብ አባታዊ (patriarchal) ሥርዓት ስር በነበረበትና ከቅርብ አሥርት ዓመታት ወዲህ እየተጧጧፈ የመጣው እንስታዊ ንቅናቄና ትወራ ሳይዳብር አስቀድሞ ኢትዮጵያውያኑ አሰላሳዮች ስለሴት ልጅ እኩልነት ወንድ ለሴት ሊያደርግ የሚገባውን ሴትም በበኩሏ ልትፈጽማቸው የሚገባትን ነገሮች በእኩልነት ላይ ተመስርተው መርምረዋል። ዘርዓ ያዕቆብ በጋብቻ ሕይወት፣ በንብረት መዝገብ፣ በአብሮነት ኑሮ፣ በስራ ክፍፍል፣ በጊዜ-ሩካቤና የወር አበባ፣ በጋብቻ አንድ-ለአንድ ስለመወሰን አዎንታዊ እይታን ያንጸባርቃል። ወልደ ሕይወት "የሩካቤን ጣዕም ከሚስትህ ጋር ተካፈለው እንጂ ለብቻህ አትሻው" (ዳንኤል፣ 2007፣ ገጽ 52) ይለናል። በትዳር ውስጥ የሚፈጸም ሩካቤ ሳይቀር በእኩልነት መጠን የሚፈጸም ጉዳይ እንጂ ወንዱ ብቻውን ለግሉ እርካታ የሚፈጽመው፣ አንዱ ብቻውን የሚደሰትበት አለመሆኑን ያሰምርበታል። እነዚህ ፍልሱፋን የሴትን እኩልነት ከእንስታዊነት ንቅናቄ በፊት አቀንቅነዋል።

ነገር ግን፣ ወልደ ሕይወት እንደ ዘርዓ ያዕቆብ የሴትን እኩልነት ለማመን ቢችልም፣ ከመምህሩ ተለይቶ ግን ለሴትነት አሉታዊ እይታን ሲያንጸባርቅ ተስተውሏል። ደቀ መዝሙሩ ወልደ ሕይወትም በሴትና

ወንድ እኩልነት ያለ ልዩነት ከሚያራምደው መምህሩ ጋር መሳ ለመሳ ይሄዳል፡፡ ነገር ግን በተጻራሪው ሴትን ደካማና ስሜታዊ አድርጎ ከብዙኃኑ አፍቃሬ-ወንድ አቀንቃኞች ጋር በአንጻሩ ይዛመዳል፤

> ትዕቢት እንዳይዛት መልከ መልካምና ከበርቴ የሆነች ሴት አታግባ፡፡ የአውስቦ ፍቅር ከትዕቢት ጋር አይስማማም እና፡፡ ሴትም እንዳይንቃትና ወደሌላ እንዳይሄድ ትዕቢተኛና ኃይለኛ ወንድ አታግባ፡፡… ወንድና ሴት ከተጋባችሁ በኋላ አንድ እንጂ ሁለት ሥጋ አይደላችሁምና እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፡፡ ከእንግዲህ ሌላ ወንድና ሌላ ሴት አትውደዱ፤ ነገር ግን አንዱ ለሁለተኛው በፍጹም ፍቅር እና በተቻላችሁ ሁሉ ደስ አሰኙ፡፡
>
> (ዳንኤል፣ 2007፣ ገጽ 61)

በእርግጥ ወልደ ሕይወት ሴትን በነቀፈበት አናቅጽ ወንድንም ተችቷል፡፡ መልከ መልካም እና ከበርቴ የሆነች ሴት ትዕቢተኛ ናት የሚል ትርጓሜ ያለው ሃሳብ ነው፡፡ እዚህ ላይ ሴትን ተቼ ቢመስልም ቅሉ፤ በአንጻሩ ወንዱንም ተችቷል፡፡ ትዕቢተኛና ኃይለኛ ወንድ ሊንቃት ወደሌላ ሴትም ሊመለከት ይችላልና ለሴቷ የትዳር ምርጫዋ እንዳይሆን ይመክራል፡፡ በሁለቱም ወገን የተመለከተውን ድክመት ሲነቅስ ይታያል፡፡ በመሆኑም የሴትን ከወንድ እኩል መሆን ያብራራበት እሳቤው እንደመምህሩ ዘርዓ ያዕቆብ እስከመጨረሻው አብሮት አልፀናም፡፡ የኢትዮጵያውያኑ ፈላስፎች የዘመን-ጓድ የሆኑ አብዛኛዎቹ የምዕራቡ ዓለም ፈላስፋዎችና ጸሐፍት በአባዊ (patriarchal) ተጽዕኖ ስር ወድቀው ሴትነትን በአቃለሉበት ወቅት፤ እንስታዊ ንቅናቄዎች ከመደርጀታቸው ከብዙ ዓመታት በፊት፤ የኢትዮጵያ ጽሑፋዊ ፍልስፍና ለሴትነት ዋጋ ሰጥቶ እንደ ነበር ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብና ሐተታ ወልደ ሕይወት በተሰኙ ሁለቱ የፍልስፍና ሐተታዎች (treatises) ማሳያነት መደምደም ይቻላል፡፡

## ማጠቃለያ

በግእዝ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ *ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብ፣ ሐተታ ወልደ ሕይወት፣ መጽሐፈ ፈላስፋ ጠቢባን፣ ፊሳልጎስ፣ ስክንድስ* የተሰኙ ፍልስፍናዊ መጻሕፍት አሉ፡፡ በእነዚህ የጽሑፍ ውጤቶች ውስጥ ጥልቅ ሐሳቦች እና የፍልስፍና ርዕዮቶች ተንጸባርቀዋል፡፡ ከመጀመሪያዎቹ ሁለቱ በስተቀር ሌሎች ኢትዮጵያዊ ለዛ ይዘው በውርስ ትርጉም ታሽተው የቀረቡ ናቸው፡፡ ዘርዓ ያዕቆብና ደቀ መዝሙሩ ወልደ ሕይወት ለሰው ልጆች የማሰላሰል ታሪክ አይነተኛ ፋይዳ አበርክተዋል፡፡ ለሀገራችን ፍልስፍና ፈር ቀዳጆች ናቸው፡፡ ዘርአ ያዕቆብ በኢትዮጵያ ጥንታዊዉ የትምህርት ሥርዐት የተማረ ሊቅ ነው፡፡ በአብነት ትምህርት በተለያዩ ደረጃ የሚሰጡ ትምህርቶችን ያጠና ነው፡፡ ዘርዓ ያዕቆብ

ክርስቲያን ፈላስፋ ነው፤ የነበረበትን ዘመን ሃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሥነ ምግባራዊ አስተሳሰቦችን በአመክንዮ ይመረምርና ያሄስ ነበር። ዘርዓ ያዕቆብ በፍልስፍናው አያሌ ነገሮችን መርምሯል፤ የፈጣሪንና ሰው ሰራሽን ህግ፣ የተፈጥሮን ሥርዓት፣ ሰው ሰራሽን ስርዓት፤ ስለፈጣሪ እንዲሁም በሃይማኖቶች ውስጥ ስለሚገኙ ህግጋትና ክፍፍሎች፣ ስለተፈጥሮ፣ ስለመለኮት እና መሰል ይዘቶች መርምሯል። አመክንዮ መር (rationalist) ፈላስፋ ስለሆነ ለዘርአ ያዕቆብ የዕውቀት ምንጭ ምክንያት (reason) ነው። ዘርአ ያዕቆብ ዕውቀትን በምክንያት ሊያገኛት ይዋትታል። ምክንያትን ዕውቀትን ለማግኘት ተጠቅሞበታል። የዕውቀት ምንጭ እግዚአብሔር እንደሆነ ያምናል። አእምሮውን በመጠቀም የሰው ልጅ መርምሮ ከእውነታው ዘንድ መድረስ አለበት ብሎ ያምናል። ዘርዓ ያዕቆብ ከምዕራቡ ዓለም ዘመናዊ ፈላስፎች ከእነዴካርት ተነጻጽሯል። በኢትዮጵያ የዘመናዊ ፍልስፍና መስራችም ነው። ፈላስፋዉ ወልደ ሕይወት (ምትኩ) የእንፍራንዝ ተወላጅ፣ የዘርአ ያዕቆብ ደቀ መዝሙር ነው። ምትኩ ዘርአ ያዕቆብ ትምህርቱን የገለጸለት ብቸኛ ተማሪ ነው። ዘርዓ ያዕቆብ ካስተማራቸው የሃብቱ ልጆች ውስጥ የዘርአ ያዕቆብን መንገድ መከተል የቻለውም እርሱ ነው። ፈላስፋዉ ወልደ ሕይወት ፍልስፍናዉ ከመምህሩ ጋር በአብዛኛው ተመሳሳይነት አለው፤ እንደዘርዓ ያዕቆብ ሁሉ የዕውቀት ምንጭን ምክንያት እንደሆነ አድርጎ የሚመረምር ነው። እንደመምህሩ ሁሉ ወልደ ሕይወትም የእውቀት ምንጭ እግዚአብሔር ነው ብሎ ያምናል። ወልደ ሕይወት አንድን ሁነት በደፈናው ከመቀበል በፊት ምክንያትን ያስቀድማል። በእምነት ከማስረገጥ በፊትም ምክንያትን ያስቀድማል፤ ከእምነት በፊት በአንክሮ መመርመር። ሁለቱ ፈላስፎች ስራቸው ከሥነ ዕውቀት፣ ዲበአካላዊ ፍልስፍና፣ ሥነምግባር፣ ሥነአመክንዮ አንጻር የሚቃኝ ነው።

## ዋቢ መጻሕፍት


ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ (ሊቀመዘምራን)። (1953)። *አንጋረ ፈላስፋ፤ የፈላሰስፋዎች አነጋገር*። አሳታሚና ቦታ ያልተገለጸ።

ሮዳስ ታደሰ (መጋቤ ሃዲስ)። (2010)። *ፊስአልጎስ*። አዲስ አበባ፡- አሳታሚ ያተገለጸ።

ብርሃኑ ድንቄ። (1987)። *አልቦ ዘመድ*። አዲስአበባ፡- አሳታሚ ያተገለጸ።

አማኑኤል መንግስተአብ (መጋቤ ሐዲስ)። (2011)። *የስክንድስ ዝምታ*። አዲስ አበባ፡- አሳታሚ ያተገለጸ።

ኤፍሬም ስዩም። (2006)። *ተዋነይ፤ ብሉይ የግእዝ ቅኔያት ፍልስፍና*። አዲስ አበባ፡- ሻማቡክስ

ዳንኤል ወርቁ (አሰናጅ)። (2007፣4ኛ ዕትም)። *ሐተታ ዘርዓ ያዕቆብ እና ሐተታ ዘወልደ ሕይወት*። አዲስ አበባ፡- አሳታሚ ያተገለጸ።

ዳንኤል ወርቁ (አሰናጅ)። *የኢትዮጵያ ፍልስፍና፡ ሐተታዘርዓያቆብ እና መጽሐፈ ጨዋታ ስጋዊ ወመንፈሳዊ* (አሳታሚና ጊዜው ያልተገለጸ)።
ዳዊት ግርማ። (2011)። እንስታዊነት በኢትዮጵያ ፍልስፍና፤ ሐተታ ዘርአ ያዕቆብና ሐተታ ወልደ ሕይወት እንደማሳያ። *ERJSSH* 6(1), Pp. 33-40
ጌታቸው ኃይሌ (ተርጓሚ)። (2006)። *ሐተታ ዘዘርዓ ያዕቆብ በመባል የሚታወቀው የወርቄ ታሪክ*፡ ኮሌጅቪል (ሚኒሶታ)።
ጎርጎርዮስ (አባ)። (1974)። *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ*፡ አዲስ አበባ፡- ትንሳኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት።
Adamu, A and Belaynesh, M. (1970). The Role of the Ethiopian Orthodox Tewahdo Church in Literature and Art. In Taddesse Tamrat and Sergew Hable Selassie (Eds.). *The Church of Ethiopia: A Panorama of History and Spiritual Life.* (pp.45-49). Addis Ababa: B.S.P.E.
Cox, P. (1983). 'The Physiologus: A Poiēsis of Nature. Church History, 52(04), 433. https://doi:10.2307/3165564
Branden, N. (1969). *The Psychology of Self-esteem: A New of concept of Man's Psychological Nature.* New York: Bantam Books.
Bender, M.L., Hailu F., and Roger, C. (1976). *Two Ethio-Semetic Languages.* Cambrige: Cambrige University Press.
Scott, A. (1998). The Date of the Physiologus. *Vigiliae Christianae*, 52(4), 430—441. https://doi.org/10.2307/1584835
Sumner, C. (1998). African Philosophy. *Ethiopian Studies Seminar Proceedings*. Addis Ababa: IES.
Sumner, C. (1981). *ዜና ስክንድስ ጠቢብ = The Life of Skendes the Wise - Critical Edition of the Ethiopic Text of Athens Secundus*. Addis Ababa: Commercial Printing Press
Taddesse Tamrat.(1970). Hagiographies and the Reconstruction of Medieval Ethiopian History. *Rural Africana*, 11(1), 12-20.